ትዝብት ቁ.19

ሰኔ 13 ቀን 2005 (20-06-2013)

## ማውራትና መሥራት ለየቅል!

የሚሰሩትን ነገር ማሰብ፣ያሰቡትን ደግሞ በተግባር መተርጎም ትክክለኛና ሂደቱን የጠበቀ አካሄድ ነው።በቃላት የተገለጸ ነገር በተግባር ካልተገለጸ ጉንጭ አልፋ ወሬ ሆኖ ይቀራል።ለዚህም ነው ከተግባር በፊት ቴዎሪ፣ከቴዎሪ ቀጥሎም ተግባር በመሆን ሳይነጣጠል አንዱ አንዱን ተከትሎ ለፍሬ የሚበቃው።

በረጋ መንፈስና በሰከነ አዕምሮ ማሰብ ከዚያም በተግባር መግለጽ ከሚፈልጉት ግብ ያደርሳል።አንድ ሃሳብ ከሌላው ወይም ከራሳችን ሊፈልቅ ይችላል፤ያንን በተግባር ለመግለጽ ግን የየአንዳንዳችን ውሳኔ ነው። እኛ አምነን የተቀበልነውን ሌላው ካለ በቂ ትንተናና አጥጋቢ ምክንያት ሊያስቀለብሰን አይገባም። የማናምንበትንም ከሌላው ለመምሰልና ለመቀራረብ ስንል ማግበስበስ አይኖርብንም። በአቋማችን የማንረጋ፣ በሌሎች ፍላጎት የምንዋልልና የምንንቀሳቀስ ከሆነ፣ ጭንቅላታችን ሌሎች የሚያዙበትና የፈለጉትን ሊያሰፍሩበት የሚችሉበት ሰሌዳ፣አንደበታችንም የሌላውን ተቀብሎ የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶ በአጠቃላይ ሌሎች እንደፈለጉ የሚያደርጉን አሻንጉሊቶች ነን ማለት ነው።በራሳችን ልቦና የምንመራ ሳይሆን በሌሎች ፍላጎትና ትዕዛዝ የምንወጣ የምንገባ፣በሌሎቹ ሳንባ የምንተነፍስ ነን ማለት ነው።ሲጣሉ የምንጣላ፣ሲፋቀሩ የምንፋቀር፣አድርግ ሲሉን የምናደርግ አታድርግ ሲሉን የማናደርግ ከሆን አሽከሮች እንጂ እኛ የራሳችን ስሜትና ፍላጎት ባለቤቶች አይደለንም ማለት ነው።ለምን ብለን ሳንጠይቅና ሳናምንበት በሌሎች ፍላጎት ሆ የምንል ከሆነ በጭፍን የምንሰግር ጭፍራዎች ነን ማለት ነው።

የዚህ ጽሁፍ መነሻ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ላይ የደረሰውን መከራና ስጋት አስመልክቶ በየቦታውና በየቀኑ ተመሳሳይ እሮሮና ብሶት እያሰማን ግን በቃላት የምናስተጋባውን ቢጋራ ቆመን በተግባር ለመግለጽ አለመቻላችንን ለመግለጽና የታዘብኩትን ድክመቶች በመጠቆም እርማት ተደርጎ ለተሻለ ውጤት እንድንነሳ ለማሳሰብ ነው።

ለምናደርገው የጋርዮሽ ተግባር እርግጥ ነው አስተባባሪና መሪ የሚሆን ግለሰብም ሆነ ቡድን ያስፈልጋል።ግን እንዲያስተባብረን የምንሻው ፍላጎታችንን ተከትሎ እንዲመራ እንጂ በራሱ ፍላጎት የሚያሽከረክረን መሆን የለበትም።

የአገር ጉዳይ የአንድ ወይም የተወሰነ ስብስብ ጥያቄና አላፊነት አይደለም፡፤ሁሉም ዜጋ እኩል የዜግነት ድርሻ አለው። እያንዳንዱ በሚችለውና ባመነበት መንገድ፣የድርሻውን ያበረክታል።

በየአቅጣጫው "አገራችን ልትጠፋ ነው" እያልን እንጮሃለን። ሌላም ሌላም ተጨምሮበት በየስብሰባውና፣በየፓልቶክ ሩም የምናሰማው እሮሮ ጆሮ ያደነዝዛል።አገር ሲጠፋ እንዴት ተቃዋሚ ነን የሚሉት ድርጅቶች በአደባባይ ወጥተው ድምጻቸውን አያሰሙም?ምን እስኪመጣ ድረስ ነው የሚጠብቁት?ሁሉም ፈሪ ሆነ፣ደፋር ጠፋ፣ጥቅም ገዛው....ወዘተ የተለመዱ ትችቶች ናቸው።በገሃድ የሚታየውና የሚያስገርመው ግን እኛ ሌሎቹን ሆኑ ብለን የምንለውን እየሆን መምጣታችንን አለማወቃችን ነው።በአገር ቤት ያሉት፣ለአደጋ የተጋለጡት አደባባይ ወጥተው አልተቃወሙም ስንል እኛ በአደባባይ በተለይም ነጻነት ባለበት አገር፣የፖሊስ ዱላ ሳያርፍብን ድምጻችንን አሰምተን ለመግባት በምንችልበት አገር እየኖርን፣ለመደራጀት አቅምና ሙብት ሳናጣ፣በልዩነታችን ላይ በግልጽ መወያየትና በሚያስማሙን ላይ ተባብረን በአንድነት ለመቆም እየቻልን የሚያመረቃ ሥራ ሳንሰራ እንዲሁ በወሃ ቀጠነ እየተባላን ዕድሜአችንን ልንፈጀው ነው።

ከአገር ጉዳይ ይበልጥ የምንከተለው ወይም የምንደግፈው ድርጅት የበላይነት እንዲኖረው፣ሙያችንና ዕውቀታችን ለሌላው አገልግሎትና ጥቅም ከሚሰጠው ይልቅ የራሳችንን ጥቅም ማስጠበቂያ አድርገን በማየት ከሌላው ጋር ለመተባበር የማንችልበት የግንብ አጥር ፈጥረናል።በድምጽ ባናሰማውም "ከድርጅቴ ወይም ከግል ጥቅሜ በላይ አገር የለም" የሚል መፈክር የሰፈረበት ሰሌዳ በልቦናችን ተሸክመን የምንጓዝ ይመስላል።

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ያለው ለብሰን ወይም ጠምጥመን፣በየዘፈኑና በየድግሱ ስንፎክርና ያዙኝ ልቀቁኝ ስንል ለተመልካች አገር ወዳዶችና ለመሰዋእትነት የቆረጥን ይመስላል፡፤በዛው አዳራሽ ውስጥ ስለአገር ጉዳይ ተነስቶ ለትግሉ መርጃ የሚሆን እርዳ ስንባል የማንደረድረው ምክንያት የለም።በዛው አዳራሽ ውስጥ ግን በጠጣልኝ በጠጭልኝ፣ለጉራ መቶ ኤሮ/ዶላር ስንመነዝር አይሰማንም።

ሌላውን እዚህ ላይ ትቼ በቅርቡ የታዘብኩትን ላንሳ፣

ከብዙ ዓመት በኋላ በአገራችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ በሰማያዊ ፓርቲ ግንባር ቀደምትነትና በሌሎቹ ተባባሪነት አንድ የፍርሃት ድባብ ያሶገደ ሕዝባዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ ከተማ በመደረጉ በውስጥና በውጭ ባለነው ዘንድ ከእንግዲህ የሚያቆመው የለም የሚል እድምታ አድሮብን ነበር።በየቦታውም በተመሳሳይ መልክ ትግሉ እንዲፋፋም የምንችለውን ሁሉ በህብረት ለማድረግ ቃል ገብተን ነበር።ምንም እንኳን ከዚያ በፊት በየአገሩ የተደረጉ የተቃውሞ ሰልፎችና ስብሰባዎች መኖራቸው ባይካድም ከግንቦት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.በኋላ የሚኖረው ሁኔታ በጥልቀትም በጥራትም እያደገ ይመጣል የሚል ግምት በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ተከስቶ ነበር።እንደተባለውም አንገት ቀና ቀና ማለት ጀመረ።በአሜሪካ፣በአውሮፓ በተከታታይ ሰላማዊ ሰልፎች ተደረጉ።የአስተባባሪ ቡድኖችም (Task forces )ተቋቋሙ።እንቅስቃሴው በቀጣይነት እንዲካሄድ ስምምነት ተደረገ፣ስልትም ተነደፈ።በዚህ መልክ በአሜሪካ በዋሽንግተንና በኒው ዮርክ ከተማዎች ካለፉት ጊዜያቶች በተለዬ መልክ ብዙ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ተካሄደ፤ለመንግሥትና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶችም የአቤቱታ ደብዳቤዎች በተመረጡ ተወካዮች አማካኝነት ተሰጠ።በአውሮፓም እንዲሁ በየአገሩ ከሚደረገው የተናጠል ትግል ባሻገር ከሁሉም አገሮች የመጡ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ቤልጅየም ዋና ከተማ በብራሰልስ ተደረገ፣የአቤቱታ ደብዳቤም ለአውሮፓ ፓርላማ ተሰጠ።

በነዚህ በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የተደረጉትን ሕዝበ እንቅስቃሴዎች ለማያያዝና ይበልጥ ለማጠናከር ብዙ እቅድ ወጣ።ሁሉም እንደገና ልቡ ተቀሰቀሰ።የሚቀጥለው ሰልፍና ትግል የበለጠ እንደሚሆን የብዙሃኑ ፍላጎትና ተስፋ የተጣለበት ነበር። የተጀመረው በተከታታይ ይቀጥል የሚለው ጥሪ በየቦታው ተሰማ።

ያ ሁሉ ምኞትና ተስፋ አሁን ውሃ የፈሰሰበት ይመስላል።ትግሉን ከቆመበት ለማስቀጠል በሚደረገው ሙከራ ላይ ያ የተለመደ የቡድንና የድርጅቶች ከይሲ በሽታ እየተጠናወተው መጣ።በአስተባባሪዎቹ መካከል አለመግባባት እየተከሰተ አንዳንዶቹ ከተመደቡበትና እንሠራለን ብለው ቃል ከገቡበት አደራ እያፈነገጡ በቤታቸው ተቀመጡ፤ትግሉን አዳከሙት።ለብዙሃኑና ላገራቸው ከሚሰጡት አገልግሎት ይልቅ ለድርጅታቸው ወይም ለቡድን ከዛም ባነሰ ደረጃ ለግለሰብ የሚያበረክቱት ታማኝነትና አገልግሎት ቀፍድዶ ያዛቸው።እኛ ካልመራነው፣እነገሌ ባዘጋጁት፣እገሌና እገሊት ባሉበት...ወዘተ የሚሉ ደካማ ምክንያቶችን እየደረደሩ ሰልፍ ላለማዘጋጀትና ላለመካፈል ወሰኑ።

በአሜሪካ ተከታታይ ሰልፎችን ካዘጋጁት መካከል አንዳንዶቹ በስበብ ባስባቡ እራሳቸውን እንዳገለሉ ይሰማል፤ በአውሮፓውም እንቅስቃሴውን ለመምራት የተመደቡት ሰዎች አደራቸውን ዘንግተው የገቡበት ቃል ኪዳን ስምምነቱ ሳይደርቅ እንደ ግመል ሽንት የኋሊት ሲሄዱ ለመታዘብ ችያለሁ።የዛሬ ወር በሜይ 15 ቀን በብራሰልስ በሚገኘው የአውሮፓ ህብረት ጽ/ቤት ደጃፍ በተደረገው ሰልፍ ከያገሩ የተሰባሰብን ከመቶ የማናንስ ሰዎች ድምጻችንን ለማሰማት የቻልነው በዚሁ በተዋቀረው አስተባባሪ ኮሚቴ ጥረት ነበር።በዚህ ስብሰባ ወቅት ከወር በኋላ ማለትም በ19 ጁን የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስቴር የሆነው ሃይለማርያም ደሳለኝ ስለሚመጣ ሃይላችንን አስተባብረን በበለጠ ዝግጅት ሰልፍ ለመውጣት ጥሪ እንደሚተላለፍ ተነግሮ ነበር። የጥሪው መልእክት ሳይሰራጭ ቀኑ እየተቃረበ መጣ፡፤ያዘጋጃሉ ብዬ የማስባቸውን ሁሉ በስልክ ብጠይቅም መልሱ አላውቅም ሆነ።ለሰልፉ ሰዓታት ሲቀሩት አንዱ ወዳጄ ደወለና እንሂድ አለኝ።ሰልፉ እንደሚካሄድ አሳመነኝና እሺ ብየው በማግስቱ ተቃጥረን አብረን የቤልጅየምን መንገድ ተያያዝነው። ከሰዓቱ በፊት ደረስን።ስንደርስ ጥቂት ኢትዮጵያውያንን አገኘን፤ሰላምታ ተለዋውጠን ሌሎቹን ለመጠበቅ ወሰን።ይመጣሉ የተባሉት ብቅ ሳይሉ ቀሩ። ከጣልያን፣ ከጀርመን፣ከሆላንድ፣ ከሉክሰምበርግ፣ ከቤልጅየም ልዩ ልዩ ቦታ ተጉዘን በቦታው የተገኘነው ሰዎች ቁጥር ከ25 አልበለጥንም።ሌላው ቀርቶ ያለፈውን ሰልፍ ያዘጋጁት በከባቢው በቤልጅየም የሚኖሩት እንኳን አልተገኙም። እንደሰማሁት ከሆነ አንዱ የሌላው ደጋፊ በመሆን በፈጠሩት አለመግባባት በአገር ላይ የተደረገ አድማ መሆኑን ነው። በቦታው ላይ የተገኙትን የአብዛኛዎቹን አዝማሚያ ሳየው የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም ደጋፊነታቸውን ልገነዘብ ችያለሁ።አብዛኛዎቹ የሚተዋወቁ  ናቸው።እኔም ሆንኩኝ ሌላዎቹ መቶ በመቶ የሚስማሙ አይደሉም፣በተለያዩ ጥያቄ ላይ የተለያየ አቋም አለን፤ግን በአገር አንድነትና በዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ አንድ አይነት ፍላጎትና አቋም ይዘን ስናንጸባርቅ ውለናል።በዚያን ወቅት የየትኛውም ድርጅት ስም አልተጠቀሰም የፕሮፓጋንዳ ወረቀትም አልተበተነም።ሁሉም ከድርጅትና ከቡድን ጥቅም ይልቅ የአገር ጉዳይ በማስቀደም በመቶዎች የሚቆጠር ኪሎሜትር ተጉዞ ሲጮህ ውሎ የተፈቀደለት ሰዓት ሲጠናቀቅ ወደየመጣበት ተመልሷል።

በዚህ ድምጻችንን ባሰማንበት አደባባይ ላይ የውጭ አገሯ ተወላጅ የአውሮፓ ፓርላማ አባል የሆነችው ወ/ሮ አና ጎመዝ ለተወሰነ ጊዜ በመካከላችን ቆማ አብራ እጇን አንስታለች፣ የእንግሊዝኛ መፈክር አስተጋብታለች።ታዲያ የጉዳዩ ባለቤቶች የሆነው በየቤታችን መሽገን መቀመጡ ለህሊናችን አይከብደንም?ሌላው ቀርቶ በትግሉ ብዙ ልምድ ያላቸውና ምሳሌ መሆን የሚገባቸው ግለሰቦች እንኳን በቦታው ብቅ አላሉም።ያሳዝናል!  የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች  በሰላማዊ

ሰልፍ መሳተፍ ደረጃቸውን ዝቅ የሚያደርግባቸው የሚመስላቸው ሆኖ ይሰማኛል።የነሱ የትግል ሜዳ በአዳራሽ ውስጥ በመድረክ ላይ ተቀምጦ መለፍለፍ ነው። ወይም በመንግሥታቱ ባለሥልጣኖችና የፓርላማ አባላት ቢሮ ደጃፍ ማንዣበብ ነው።ከሕዝብ ጋር አብሮ ያልዋለ፣ድምጹን በአደባባይ ያላሰማ ፣ከቶ የሕዝብን ፍላጎትና መብት ለማስጠበቅ መስዋዕት ይሆናል ብሎ ለማመን ያዳግታል።ለትንሿ ፈተና ያልቀረበ ለትልቁማ እንዴት?

ሌላው ደግሞ በስደተኛ ስም መኖሪያ ፈቃድ ያገኘው ፣ከኢትዮጵያ በማስመጣት እንጀራ፣ሽሮና በርበሬ እየነገደ በአገር ቤት ላለው ወይም ወደፊት ይኖረኛል ብሎ ለሚያስበው ጥራቱን ላልጠበቀ ግን ከሚገባው በላይ ገንዘብ ለሚከፍልበት ኮንደሚኔም ቤት ቅድሚያ እየሰጠ ያገሩን ጉዳይ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኗል።እዚህ ላይ ያልተረዳው ነገር ቢኖር አሁን በተያዘው መንገድ አገር እንደማይኖር፣አገርም ሳይኖር  እንኳን ቤትና ንብረት ለመያዝ ቀርቶ ለእረፍትም ሄዶ ለመመለስ ዕድሉ እንደማይኖርና እንደማይቻል ነው።ለእውነት፣ ለእኩልነትና ለመብት መቆም፣ለሕጋዊ ስርዓት መታገልና ለዚያም መብቃት የራስን ሃብትና መብት በዘለቄታዊነት ማረጋገጥ እንደሆነ ልብ ሊለው ይገባል። በተጨማሪም ብዙ ንብረትና ቤት ያላቸው ሰዎች በአገራቸው መሬት ላይ ሰላምና ዴሞክራሲ ሰፍኖ ማየትን ስለሚመርጡ ንብረቴን እቀማለሁ ወይም አጣለሁ ሳይሉ በአደባባይ እየወጡ የሕዝቡን ብሶት በማሰማት እንደሚሳተፉ እያዩ መረዳት ከፍርሃት ሰንሰለት ነጻ ያደርጋል። ልሳኑን ዘግቶና አንገቱን ደፍቶ እንደውሻ የሚወረወርለትን ከማፈንፈን  ይልቅ በነጻነት አንገቱን ቀና አድርጎ በሰውነት ደረጃ መብቱን አስከብሮ የሚያገኘው ሃብትም ሆነ ንብረት የበለጠ ዋስትና አለው ፤በራስ የመተማመኑንም ደረጃና ስሜት ከፍ ያደርገዋል።በትግል ውስጥ ለአደጋ ቢጋለጡም፣ የሃብት ጥቅም ባይገኝበትም ለሃቅ መቆም በገንዘብ የማያገኙትን የህሊና እርካታ ይሰጣል።

ለማጠቃለል ያህል በየቦታው የተቋቋሙት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የተፈጠሩበትን ጉዳይ አጢነው ሕዝብ የሰጣቸውን አደራ እንዲወጡት ያስፈልጋል እላለሁ።ለየድርጅቶቻቸው ወይም ለሚከተሉት ሰው የሚሰጡትን አገልግሎትና ታማኝነት ለማሳየት ሲሉ የብዙሃኑን ፍላጎት ገደል ባይከቱት ለነሱም ለድርጅታቸውም ለቡድናቸውም መልካም ይሆናል።ምንም እንኳን የአመለካከት ልዩነት ቢኖርም በአገር ጉዳይና በጋራ ጥያቄ አብረው ሊሰለፉ ይገባቸዋል።

በድርጅት ፍቅርና ታማኝነት ሲሉ የብዙሃኑን የጋራ ትግል የሚያዳክሙ ሰዎች የማይታረሙና በዚሁ ሥራቸው የሚቀጥሉበት ከሆነ  በምትካቸው ቃላቸውን የሚያከብሩና ሃላፊነትን የሚወጡ ሰዎች ተተክተው ትግሉ እንዲቀጥል የማድረግ አላፊነት የብዙሃኑ ነው። አስተባባሪ ጠፋ ብሎ ተስፋ መቁረጥና መዳከም አይኖርበትም።

ወሬ በሥራ ይተርጎም!

ቡድናዊነት ይቁም!

አገሬ አዲስ